# እያንዳንዱ የሐረሪ ብሔረሰብ ተወላጅ ለእውነተኛ ታሪኩ ዘብ ይቁም!!

**አሚር ኑር ቀለም** 12-17-14

የአሹራ በዓል አከባበር ሥነ-ሥርዓቶች አንዱ የሆነውን ውርሻቶ በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ ለተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣የሣይንስና የባህል ድርጅት የቀረበው ጥያቄ ተቃውሞ ማስነሳቱ ሰሞኑን ሡፊ የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን ከተሰጣቸው ሀገራዊ ጉዳዮች አንዱ ሊሆን ችሏል፡፡ የጀርመን ድምፅ የአማርኛ ፕሮግራም ክፍል በዚሁ ጉዳይ ላይ አቶ ዮናስ ደስታን አነጋግሯል፡፡ ሪፖርተር ጋዜጣም በሕዳር 24 ቀን 2007 ዓ.ም ዕትሙ በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብ የተጠየቀው የ«አሹራ» በዓል አከባበር ይዘት ተቃውሞ ማስነሳቱን ዘግቧል፡፡ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሚኖሩ የሐረሪ ብሔረሰብ ተወላጆች በበርካታ ማኅበራዊ ድረ ገጾችም ይህንኑ ጉዳይ የመወያያ ርዕስ አድርገውታል፡፡

እኔም በብሔረሰቡ ተወላጅነቴ ከሁለት ዓመት በፊት መከታተል ጀምሬ በመካከሉ የተስተካከለ መስሎኝ ያቋረጥኩትን ጉዳይ እንደገና ለመከታተል ተገፋፋሁ፡፡ ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝም ይኸው የብሔረሰቡ ተወላጆች ውይይት ነው፡፡ በመሠረቱ የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የብሔረሰቡን ባህልና የታሪክ ቅርሶች የመንከባከብ ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣለት ያዋቀረው የባህል፣ የቅርስ ጥበቃና የቱሪዝም ቢሮ የሐረሪ ብሔረሰብን የአሹራ በዓል አከባበር በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ ጥረት ማድረጉ የሚያስ መሰግነው እንጂ የሚያስወቅሰው አይደለም። በዚህ ጉዳይ ተቃውሞ ያለው ሰው ይኖራል ብዬ አላምንም፤ ቅሬታው በዓሉ ለምን የዓለም ቅርስነት ታጨ የሚል አልነበረም፤ አይደለምም፡፡ አንባቢ ታዲያ ይህን ቅሬታ ያስከተለው ችግር ምንድን ነው ? ብሎ መጠየቁ አግባብ ይሆናል፡፡

ስለዚህ አንባቢ በእርጋታ የብሔረሰቡ ተወላጆች ምሬት መንስዔ የሆነውን ጉዳይ ለመረዳት እንዲችል በመጀመሪያ የአሹራ በዓልን ምንነትና የሐረሪ ብሔረሰብን የአሹራ በዓል አከባበር ሥነ ሥርዓት ባጭሩ እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡ በእስላማዊ የቀን አቆጣጠር የዓመቱ የመጀመሪያ ወር ሙሐረም ይባላል፡፡የሙሐረም ወር አሥረኛው ቀን ደግሞ አሹራ ተብሎ ይጠራል፡፡ ሙስሊሞች ይህንን ቀን በየዓመቱ ያከብራሉ፡፡ምክንያቱም አሹራ አላህ ለአደምና ለሐዋ ይቅርታ ያደረገበት፣ ነቢዩ ኑሕ ከጥፋት ውሃ ድነው ከመርከባቸው ወደ ምድር የወረዱበት፣ ነቢዩ ኢብራሂም በሰደድ እሳት ከመቃጠል የዳኑበት፣ ነቢዩ ሙሳ የቀይ ባህርን ሰንጥቀው በመሻገር ወገኖቻቸውን ከፈርዖን አገዛዝ ነፃ ያደረጉበት፣ ነቢዩ ዒሣም የተወለዱበትና ሌሎችም የተለያዩ የአላህ ፀጋዎች የተከሰቱበት ቀን በመሆኑ ነው፡፡

በሙስሊሞች ታሪክ ውስጥ በዚሁ ቀን የተፈፀመ ሌላም ድርጊት አለ፡፡ የነቢዩ መሀመድ የልጅ ልጅ የሆኑት ሑሴይን በግፍ የተገደሉት በዚሁ ቀን ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ሙስሊሞች ይህንን ቀን በአንድ በኩል ከላይ የተጠቀሱትን የአላልህ ፀጋዎች እያሰቡ፤ በሌላ በኩል በሑሴይን ላይ የተፈፀመውን ግዲያ በኀዘንና በቁጭት እያስታወሱ በየዓመቱ ያከብሩታል፡፡

የሀረሪ ብሔረሰብም በሙስሊምነቱ በየዓመቱ የአሹራን በዓል ያከብራል፡፡ የሚያከብረውም ሦስት ተግባራትን በማከናወን ነው፡፡ አንደኛ በዕለቱ ይፆማል፤ሁለተኛ በዕለቱ ምሽት በየቤቱ ገንፎ አዘጋጅቶ ቤተሰቡና ጎረቤቶቹ እንዲመገቡ እንዲሁም በየአድባራቱም ገንፎውን ጅቦች እንዲበሉ ያቀረብላቸዋል፡፡ ሦስተኛ ወጣቶች ተሰባስበው ዱላ ይዘው «ዊርሻቶ» የሚል ዜማ እያዜሙ ቤት ለቤት ይዞራሉ፡፡ የዜማቸው ግጥም ፍሬ ሃሳብ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ከሞላጎደል ፡-

«ሸረኛ ይውጣ ይሰባበር፤

የተደበቀው የውስጥ አርበኛው ከተገኘ ይሰባበር፤

መጪው ዓመት ቸር ወሬያችሁን ያሰማን፤

አላህ ዓመቱን የተባረከ ያርግላችሁ፤

ትናንሾቹ ይደጉ፤

ታላቅ እህታችን እንደ ሐሰን እና ሁሴን የተባረኩ ልጆች ይስጥሽ፤

ውድ አያታችን ሃይማኖቱ በረካ ይሁን፤

እኛም እነዚያ ሁሴንን የገደሉትን ቤት ለቤት በየጓዳው ስንፈልግና ስናፈላልግ በትራችን ሳይቀር ደክሞታልና እርስዎም እስቲ ጓዳዎ ውስጥ ድንገት ከተደበቁ ፈልገው ያውጧቸውና ይስጡን? » የሚል ነው፡፡

የቤቱ ባለቤት የሆኑት እናትም ከጓዳቸው አውጥተው ድፍን ቅል ለወጣቶቹ ይወረውራሉ ወጣቶቹም «ሴረኛውን ሸረኛውን ብናገኘው እንደዚህ ነው የምንሰባብረው» እያሉ የተወረወረላቸውን ቅል ሰባብረው ይሄዳሉ፡፡ ወጣቶቹ ሴረኛና ሸረኛ የሚለውን ሐረግ የሚጠቀሙት ሁሴይንን የገደሉትንና ከገዳዮቹ ጋር ያሴሩትን በወቀቱም ዕኩይ ተግባራቸውን ከፈጸሙ በኋላ የተሸሸጉትን ወንጀለኞች ለማስታወስ ነው፡፡

አንባቢ ስለአሹራ በዓል ምንነትና ስለሐረሪ ብሔረሰብ የአሹራ በዓል አከባበር ሥነ ሥርዓት ከተገነዘበለኝ ለብሔረሰቡ ተወላጆች ተቃውሞ ምክንያት ወደ ሆነው ነጥብ ከመግባቴ በፊት ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ እንደሚባለው ጉዳዩን የበለጠ ለመረዳት ይጠቅማልና ከሁለት ዓመታት በፊት የተፈጠረውን አንድ ክስተት በአስረጂነት እጠቅሳለሁ፡፡ የዛሬ ሁለት ዓመት በወቅቱ የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህል፤ቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም ም/ቢሮ ኃላፊ የነበሩት አቶ አዩብ ፈቂ ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሐረሪ ብሔረሰብ የአሹራ በዓል አከባበር ሥነ ሥርዓት መካከል አንዱ የሆነውን ወጣቶች ተሰባስበው ዱላ ይዘው ዊርሻቶ የሚል ዜማ እያዜሙ ቤት ለቤት እየዞሩ የሚወረ ወርላቸውን ቅል የሚሰብሩበትን በዓል አስመልክተው በሰጡት መግለጫ የሚከተለውን ብለው ነበር፡፡

«በአንድ ወቅት የነበረ የሐረሪ ዐሚር የሕዝቡን ሁኔታ በቀጥታ ለመከታተል ራሳቸውን እንዳይታወቁ በመሸፋፈን ከተማውን ሲዞሩ አንዲት ትንሽ ሴት ልጅ ሕፃን ተሸክማ ሲትሄድ አዩዋትና የተሸከምሽው ልጅ የማነው ብለው ይጠይቋታል፡፡ እሷም አባቴ ሰክሮ ደፈረኝ፡፡ ስለዚህ ልጁ የአባቴ ነው ብላ ነገረቻቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ዐሚሩ መጠጥ እንዳይጠጣና መጠጫዎቹም እንዲሰባበሩ አዘዙ፡፡ ስለዚህ የቅል ሰበራው የሚካሄደው በወቅቱ ዐሚሩ በሰጡት ትዕዛዝ መሠረት ነው፡፡»

በወቅቱ አቶ አዩብ ፈቂ የሰጡት መግለጫ ብዙዎቻችንን አደናገረን፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ወጣቶች ተሰባስበው ዱላ ይዘው ዊርሻቶ የሚል ዜማ እያዜሙ ቤት ለቤት የሚዞሩበትን ምክንያት ከአንደበታቸው የሚወጡት ግጥሞች በግልጽ እያስረዱ እርሳቸው ግን ከአልኮል መጠጥና ከስካር መዘዝ ብሎም ዐሚሩ ከሰጡት ትዕዛዝ ጋር ያያዙት ከዬት አምጥተው ነው? የሚለው ጥያቄ ሁሉንም ማነጋገር ጀመረ፡፡ የርሳቸው መግለጫ የመንግሥትና የገዢው ፓርቲ አፊሴያላዊ አረዳድ ነው እንዳይባል ቅሬታው የክልሉ ገዥ ፓርቲ አባላትና የመስተዳደሩ ሠራተኞችንም ያካተተና በጠቅላላው አብዛኛዎቹን የብሔረሰቡ ተወላጆችን ያስደነገጠ ጉዳይ ሆኖ ተገኘ፡፡

በመሠረቱ ሐረሪዎች እስልምናን የተቀበሉት አልላህ እንዲፈጽሙ ያዘዛቸውንና እንዳያደርጉ የከለከላቸውን አውቀው ነበር፡፡ ከዚያ ዘመን ጀምረው አልላህ ከከለከለው እየታቀቡና ያዘዛቸውን እየፈጸሙ የሚኖሩ መሆናቸውን አባቶቻችን ያስተላለፉልን ሠነዶች ሁሉ ያስረዳሉ፡፡ አባቶቻችን ያቆዩልን የታሪክ ሠነዶች 72 አሚሮች ሕዝቡን ተራ በተራ ማስተዳደራቸውን ያመለክታሉ፡፡ ይህ አቶ አዩብ ፈቂ የተናገሩት ተረት ጽኑ ሙስሊምነቱ በበርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ታሪክ ፀሐፊዎች በተመሰከረለት ሕዝብ መካከል እንዴት ሊፈጠር ቻለ? በዬትኛው ዐሚር ዘመንስ ተከሰተ? የሚሉ ጥያቄዎች በብሔረሰቡ ተወላጅነቴ በአዕምሮዬ ውስጥ መጉላላት ጀመሩ፡፡

ቀስ በቀስም አቶ አዩብ ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሰጡት መግለጫ ታሪካዊ መሠረት የሌለውና የሕዝቡን ታሪክ የሚያጠለሽና የሚበርዝ መሆኑን ገልጸው ኃላፊነት የሚሰማቸው የብሔረሰቡ አባላት በገሀድ መናገር ጀመሩ፡፡ይህ በዚህ እያለ ጉዳዩ በክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ቀረበ ፤ውይይት ተደርጎበት አቶ አዩብ የሰጡት መግለጫ ስህተት መሆኑ በምክር ቤቱ አባላት ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ እንዲታረም ተወስኗል የሚል ወሬ በሠፊው ተነዛ፡፡ የብሔረሰቡ ተወላጆች እኔም ጭምር በሰማነው ወሬ ተደስተን ውሾን ያነሳ ውሾ ይሁን ብለን ጉዳዩን እርግፍ አደርገን ተውነው፡፡

በበኩሌ እኔም ሆንኩ በርካታ ወንድሞቼ እርማቱ ተፈጥሯና መሆን የሚገባው ነው የሚል እምነት ስለነበረን የክልሉ ምክር ቤት አስተላልፎታል የተባለውን ከላይ የተጠቀሰውን ውሳኔ ለማረጋገጥ አንዳችም ሙከራ አላደረግንም፡፡ የሌሎችን ባላውቅም

እራሴ ግን በድርጅቴ በሐረሪ ብሔራዊ ሊግ ላይ ጽኑ እምነት ስላለኝ ወሬውን በተራ አሉባልታነት ለመውሰድ አንዳችም ምክንያት ስላልነበረኝ ለማጣራት አልሞከርኩም፡፡

የአሹራ በዓል አከባበራን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ የቀረበው ጥያቄ ተቃውሞ ማስነሳቱ ከመገናኛ ብዙኀን ስሰማ ታርሚል ብዬ ያሰብኩት ግድፈት ሊሆን ይችላል ብዬ ስላልገመትኩ ደግሞ ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ ምንስ ተከሰተ?  አሰኘኝ፡፡ ከተኛሁበትም አባነነኝ፡፡ የተቃውሞውንም መንስዔ ለማወቅ ከሁሉ አስቀድሜ የአሹራ በዓል አከባበርን በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ ለተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣የሣይንስና የባህል ድርጅት ጥያቄ የቀረበበትን የማመልከቻ ቅፅ ለማግኘት ጥረት አደረኩ፡፡ ተሳካልኝና አገኘሁት፡፡

ቅፁን ሳነብ መጀመሪያው ገጽ ላይ የሚከተለው በሐረሪ ቋንቋ ተጽፎ አገኘሁ፡፡

«አሹራ ኢድ ዚሰላም ሒልቂ ኩትቤ ሜገሊታ«  ወህሪ ሙሃረምቤ አስትራ«  ኢያምቤ ዩትገደርዛል ኢድንታ፡፡ ዩ ሞይ ዚሐረሪ ወልዳች ኢጇዚዩቤ በርቲ መልሐድቤ ጋርሌ ጋር ዋ አዋቻች ኪልዋለሉ አፍዚዩቤ ዊርከቶ ኪላዩ ቁሉእ ይሰብራሉ፡፡ ዩው ዩሰብሩቦዛል ሰበብ ነቢ ሙሐመድ (ዐ.ሰ.ወ.)  ዚኸተሮ መስቻው መትቄጠብሌ ዋ አዝዞ ኩትዞም አደባሕ ዚትቂጣጠረቤ አውወል ወቅቲቤ ዚሐረሪ አሚር መስቻው መትኻተርሌ መስቸዞ ጠብ ዩልባዚናር ጋናች ዚሲባበሩቦ ሞይ መኸነዞቤ ዩ አሹራ ኢዱው ሉይ ኩትቤ ያገድሮሆል፡፡ ዲባየቤም ዩ ሞይቤ ወራበሌ ሹር ዩቀርባል፡፡ ዩም ጌይ መዲናው ዚሰላም ዋ ዚመትፈራረክ ኡሱእቤም ሑሉፍ ባየማ ኡሪባህ መትላመድዜ አለም ደረጀቤ ቲትታወቂኩት አሼ፡፡»

በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ ያለው በሐረሪ ቋንቋ የተጻፈው ከሞላጎደል የአማርኛ ትርጉሙ የሚከተለውን ነው፡፡

«የአሹራ በዓል በሙስሊም ቀን አቆጣጠር በመጀመሪያው«ሙሐረም »  አሥረኛው ቀን የሚውል በዓል ነው፡፡ በዚህ ቀን የሐረሪ ወጣቶች በእጃቸው በትር በመያዝ ቤትለቤትና በየአድባራቱ በመዞር ዊርሻቶ እያሉ ቅል ይሰብራሉ፡፡ ይህን የሚሰብሩበትም ነቢዩ ሙህመድ የከለከሉትን መጠጥ ለማስታወስ እና እንደዚሁም ከዚሁ ጋር በተያያዘ በድሮ ዘመን የሐረሪ ዐሚር መጠጥን ለመከላከል መጠጥ ይጠመቅባቸው የነበሩትን ጋኖች የሰባበሩበት ቀን በመሆኑ ይህን የአሹራ ቀን በተለየ ሁኔታ ያከብሩታል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ቀን ለጅብ ገንፎ ያቀርባሉ፡፡ ይህም ሐረርን የሰላምና የመቻቻል ከተማ ከሰው አልፎ ከአውሬ ጋር በመለማመድ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንድትታወቅ አድርጓታል፡፡»ከፍ ሲል እንደገለጽኩት እኔም ሆንኩ መላው የብሔረሰቡ ተወላጆች በአሹራ በዓል ዊርሻቶን የምንረዳበትና የታሪካችን ድርሳኖችም የቅል ሰበራው ከመጠጥ ጋር የተያያዘ አለመሆኑን ስለሚያሳዩ ይህ የአልኮሆል ውግዘት ታሪክ ለምን ተፈለገ የሚል ጥያቄ ጫረብኝ፡፡ በትረካው የተዘገበው ተጨባጭ የብሔረሰባችንን የታሪክ አተረጓጓም ለምን መከተል እንዳልመረጠም ግራ ገባኝ ምንም እንኳን በሀረሪ ቋንቋ የቀረበው ትረካ እስከዛሬ ከማውቀውና ከተዘገበው ጋር የማይጣጣም ቢሆንም አዲስ ነገር ይኖር ይሆን በማለት ሰነዱን ማንበቤን ቀጠልኩ፡፡

የክልሉ መስተዳድር በጥያቄው ማቅረቢያ ቅፅ ውስጥ ሊሞሉ የሚችሉ መረጃዎችን አሰባስቦ እንዲያዘጋጅ አንድ ቡድን አቋቁሞ እንደነበር ተረዳሁ፡፡ በዚህም መሠረት ቡድኑ ስለ አሹራ በዓል አከባበር የሚያወሱ የተለያዩ ጽሑፎችንና የቆዩ ፎቶግራፎችን ማሰባሰቡ በተጠቀሰው ቅፅ ውስጥ ሠፍሮ አገኘሁት፡፡ ቡድኑ የብሔረሰቡን አዛውንትና የሃይማኖት አባቶች ማነጋገሩ ተጠቅሷል፡፡ ቅፁ በዓሉ በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብ በሐረርና በአዲስ በአበባ የሚገኙ የብሔረሰቡ ተወላጆች ድጋፋቸውን የገለጹበትን ፊርማ ስለያዘ ደብዳቤም ያወሳል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና የኢትዮጵያ ጥናት ኢንስቲትዩት ባለድርሻ አካላት ሆነው የአሹራ በዓል አከባበርን በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ በተካሄደው የዝግጅት ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ጥያቄው የቀረበበት ቅፅ ያስረዳል፡፡

ጥያቄዬን እንደያዝኩ የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህል፣የቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም ቢሮ የአሹራ በዓል አከባበርን በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ ያደረገው ጥረትና የሌሎችም ባለድርሻ አካላት የነቃ ተሳትፎ ከልቤ እያመሰገንኩ ሠነዱን በማገላበጥ ላይ እያለሁ በጥያቄ ማቅረቢያው ቅፅ ላይ ያየሁት ጽሑፍ ከፉኛ አስደነገጠኝ የሚከተለውንም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተጽፎ አየሁ፡፡

«…The Wirshato gourd smashing ceremony the universal message assumes to reflect the core theme of Ashuras as manifested in Wirshato lines in the poem.

In the inst- ance,based on the legend established in Harari society,the drunkard indulges inappropriate evil act that gave birth to a bastard from his own mother.In the legend,it goes on that the woman herself is persistent to expose the alchol.Being the victim woman as character in the legend justifies and dares to the conemination alcohol as an evil substance…»

የእንግሊዝኛው አንቀጽ ወደ አማርኛ በቁሙ ሲተረጎም የሚከተለውን ይመስላል፡፡« የዊርሻቶ ቅል ሰበራ ሥነ ሥርዓት በዊርሻቶ ግጥም ስኒኞች ውስጥ የሚንፀባረቀው በሁለንተናዊ መልዕክት የአሹራ ዐቢይ ጭብጥ ተደርጎ ተወሰዷል፡፡ የሐረሪ ማኅበረሰብ አፈ-ታሪክ የሚያሳየው የአልኮል መጠጥ

ሱሰኛ በማኅበረሰቡ ውስጥ ተገቢነት የሌለውን ሰይጣናዊ ድርጊት ፈፅሞ ከገዛ እናቱ ዲቃላ ልጅ እንደ ወለደ ይታወቃል፡፡ በአፈ-ታሪኩ መሠረት የነውረኛ ድርጊቱ ሰለባ በመሆኗ ሴትዮዋ ራሷ አልኮልን ለማጋለጥ በአቋሟ እንደፀናችና አልኮል ሰይጣናዊ ነገር መሆኑን አረጋግጣ ለማጋለጥ እንደ ደፈረች አፈ-ታሪኩ ያትታል፡፡ »

ይህንን እያነበብኩ እጅግ በጣም ደነገጥኩ፤ ዓይኖቼንም ማመን አቃተኝ፡፡ አበው «ጉድና ጅራት ከበስተኋላ ነው» ያሉት አለምክንያት አለመሆኑ ቁልጭ ብሎ ታየኝ፡፡ በዓይነ ሕሊናዬ ወደ ልጅነት ዘመኔ ተመልሼ በየዓመቱ የአሹራ በዓል ሲከበር ከዕድሜ እኩዮቼ ጋር ስናዜም የነበረውን የዊርሻቶ ግጥሞችን ለማስታወስ ሞከርኩ፡፡ አለህም ዱሊላሂ ግጥሞቹን ፈፅሞ አልረሳኋቸውም፡፡ ልክ እንደልጅነቴ አነበነብኳቸው፡፡ በሠነዱ የመጀመሪያው ገጽ ላይ በሐረሪኛ ቋንቋ መጻፉን ጠቅሼ በግርድፉ ወደ አማርኛ የተረጎምኩትን ከዚህ በላይ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከሰፈረው ጋር አነጻጽሬ አየሁትና የባሰ ብርክ ያዘኝ

እኛ ራሳችን የብሔረሰቡ ተወላጆች በልጅነታችን በየዓመቱ እያዜምን ያደግነውንና ዛሬ ደግሞ ልጆቻችን የሚያዜሙትን የዊርሻቶ ግጥሞችና ጭብጣቸውን ለመግለጽ ዋቢ ጽሑፍ መጥቀስ ለምን እንዳስፈለገ ከቶውንም አልገባ አለኝ፡፡ በሌላ በኩል አንድ የራሱ ታሪክ በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብለት ማመልከቻ የሚያቀርብ አካል በአንድ ሠነድ ውስጥ ስለታሪኩ እንዴት ሁለት እርስበርስ የሚቃረኑ መረጃዎች ጽፎ ያቀርባል? የሚል ጥያቄ በሕሊናዬ ውስጥ አቃጨለ፡፡

ከዚህ በላይ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለሰፈረው ጽሑፍ ምንጩ አቶ ዓሊ ናጂ እ.ኤ.አ በ2012 ለንባብ ያበቁት ፅሑፍ መሆኑ ስለተገለጸ፤ይህንኑ በዋቢነት የተጠቀሰውን ጽሑፍ አፈላልጌ አገኘሁት፡፡ የአቶ ዓሊ ናጂ ጽሑፍ ሲፈተሽ ደግሞ እርሳቸውም በተራቸው ምንጫቸው እ.ኤ.አ በ1991 ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘከሪያ«Hyena porridge ethnographic filming in city of Harar.» በሚል ርዕስ ያዘጋጁት ጽሑፍ ሆኖ ተገኘ፡፡ ይህ ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ሥራ ፈጠረልኝ፡፡

እናም የረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘከሪያን ጽሑፍ ፈልጌ አገኘሁት፡፡ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እጠቅሳለሁ፣ «ቀደም ባለ ወቅት ከዕለታት አንድ ቀን በሐረሪ ሕዝብ መካከል የአልኮል መጠጥ በማህበረሰቡ መካከል ስላለው ሚና የከፋ ክርክር ተነስቶ ነበር ይባላል፡፡ ይህም ክርክር የአልኮል መጠጥ ጠቃሚ ነው በሚሉና የአልኮል መጠጥ ጎጂ ነው በሚሉ ሰዎች መካከል የተካሄደ ሲሆን፤ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ጠንካራ የመከራከሪያ ነጥቦችን አቀረቡ፡፡ ሆኖም ውሳኔ ላይ መድረስ አልቻሉም፡፡ በመጨረሻም ሁለቱም ወገኖች የአልኮል መጠጥ በህብረተሰቡ ወስጥ ስላለው ሚና ህብረተሰቡ ውስጥ ገብተው ለማጥናት ተስማሙ፡፡ ወዲያውኑም በጣም አስቸጋሪ የሆነውን የመስክ ጥናታቸውን ጀመሩ፡፡ በመንገዳቸውም ላይ ከአንዲት በጀርባዋ ልጅ ካዘለች ሴት ጋር ተገናኙ፡፡ ሴትዮዋንም አቁመው ስለ አልኮሆል መጠጥ ሚና ቃለ መጠይቅ ያቀርቡላት ጀመር፡፡ ገና የአልኮሆል መጠጥ የሚለውን ቃል ስትሰማ ዘላ ተወራጨችና በንዴት የአልኮሆል መጠጥን ማውገዝ ጀመረች፡፡ ከዚያም ቀስ ብለው ካረጓጓት በኋላ እንዴት በአልኮል መጠጥ ኃይል ተገፋፍቶ የገዛ ልጇ እንደደፈራትና ይህን በጀርባዋ ያዘለችውን ዲቃላ ልጅ ለመውለድ እንደተገደደች ተረከችላቸው፡፡ ይህ የማይታመን ክስተት በወቅቱ በነበረው ማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ ድንጋጤ ፈጠረ፡፡ የተከራካሪዎቹም ጥናት በዚሁ ተጠናቆ የአልኮል መጠጥ መያዣ ዕቃዎችንም መሰባበር ተጀመረ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ትምህርት የሚማሩ ልጆች የአልኮል መጠጥ የሚያዝባቸውን በተለይም ቅሎችን የአሹራ ቀን ከመድረሱ በፊት ከሳምንት በላይ ለሚሆን ጊዜ በመሰብሰብ በአሹራ ቀን በትምህርት ቤታቸው ቅጥር ግቢ ውስጥ በጠንካራ ዱላ ይሰባብራሉ። በመቀጠልም ከቤት ቤት በመዘዋወርም ተጨማሪ ቅሎችን እንዲጥሉላቸው በመጠየቅ እዚያው ቅሎቹን በያዙት ዱላ ይሰባብራሉ፡፡ በዚህም ሁኔታ ያረፍዳሉ፡፡» የሚል ትረካ ተጽፎ አነበብኩ፡፡

ከሁሉ አስቀድሞ ያስደነገጠኝ እንደማንኛውም ሕዝብ የሐረሪ ሕዝብ የእስልምና ሃይማኖት ተቀበሎ ወደ እስልምናም የገባው የአልኮል መጠጥን ሐራምነት ጠንቅቆ በማወቅና ባሕሉም የእስልምና ሃይማኖት በሚያዘው መንገድ የተቀረፀና በዚሁ እስላማዊ

እሴቱ እየተመራ ይኖር እንደነበረ በርካታ የታሪክ ሠነዶች የሚመሰክሩ መሆኑ እየታወቀ በህዝቡ መካከል የአልኮል መጠጥ በማህበረሰቡ መካከል ስላለው ሚና ባንድ ወቅት የከፋ ክርክር ተነስቶ ነበር የሚለው የረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ ተረት ነው፡፡ ይኽ ጤናማ አዕምሮ ያለው ማንኛውም ሰው ተቀብሎት ታሪክ ብሎ መጻፍ ቀርቶ በእውኑም ሆነ በሕልሙ ከቶውንም ያስባል ተብሎ አይገመትም፡፡

የክልሉ የባህል፤ቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አዩብ ፈቂ ከሁለት ዓመት በፊት «አባት ሰክሮ የራሱን ሴት ልጅ » ደፈረ በማለት ያቀረቡት በሌላ አዲስ ተረት መተካቱን ተገነዘብኩ፡፡ ምንጩ የአቶ ዓሊ ናጂ ጽሑፍ መሆኑ ተገልጾ « ልጅ ሰክሮ እናቱን ደፈረ » በሚል ከረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ ጽሑፍ እንዳለ የተገለበጠ ሌላ ተረት ለተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣የሣይንስና የባህል ድርጅት ጥያቄ ማቅረቢያ ቅፅ ውስጥ ተሞልቶ ማየቴ ክፉኛ አስደነገጠኝ፡፡

ሌላው ግራ ያጋባኝ ነገር ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ በጽሑፋቸው ውስጥ የዊርሻቶን ግጥሞችም በሐረሪ ቋንቋ ካሠፈሩ በኋላ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተረጉመው ሲያቀረቡ በሐረሪ ቋንቋ «አባዬ ሐሰን ዚታ ሑሴን ዚታ ሊጂ የሰጠሽ » የሚለውን ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ሲተረጎሙት « My sister,may He give a good and blessed boy » ማለታቸው ነው፡፡ የሐሰንና የሑሴንን ስም መጥቀስ ለምን ፈሩ? ምናልባት የቅል ሰበራው የሚካሄደው «በአልኮል መጠጥ ኃይል ተገፋፍቶ የገዛ ልጇ እንደደፈራትና ይህን በጀርባዋ ያዘለችውን ዲቃላ ልጅ ለመውለድ እንደተገደደች ተረከችላቸው፡፡» እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአልኮል መጠጥ የሚያዝባቸውን በተለይም ቅሎችን ወጣቶች በአሹራ ቀን መሰባበር ጀመሩ የሚለውን ተረታቸውን የሚያፋልስባቸው በመሆኑ ይሆን ?

ከእርሳቸው አጻጻፍ የምንረዳው ለተነሱበት ዓላማ የሚበጀውን የመረጣ ስልት በመከተል የተካኑ መሆናቸውን ነው፡፡ በዚህ ስልታቸውም መረጃ አጠጣም ማቅረብ፣ የሚጠቅማቸውን ብቻ አጉልቶ የማሳየት፣የማይጠቅማቸውን በመተው የዳበረ ክህሎት እንዳላቸው እንረዳለን፡፡ ከሁሉም በላይ ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ እጅግ በጣም የረቀቀ የማጠልሸት ስልት የሚጠቀሙ መሆናቸው ጎልቶ ይታያል፡፡ ረዳት ፕሮፌሰሩ የራሳቸውም የሆነውን የብሔረሰባቸውን ታሪክ ለማጠልሸት ለምን መረጡ? የሚሉ ጥያቄዎችን ለማንሳት እንገደዳለን፡፡ በግልጽ በሐረሪ ቋንቋ የተጻፈው ከላይ ተጠቀሰው ስንኝ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ከሞላጎደል «ታላቅ እህታችን እንደ ሐሰን እና ሑሴን የተባረኩ ልጆች ይስጥሽ » ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ያለአንዳች ጥርጥር ወጣቶቹ የቅል ሰበራውን ሥነ ሥርዓት የሚካሄዱት የነቢዩ መሐመድ የልጅ ልጅ የሆኑት ሑሴይን በግፍ የተገደሉበትን ቀን ለመዘከር መሆኑን በግልጽ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የክልሉ የባህል፣የቅርስ ጥበቃና የቱሪዝም ቢሮ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የተለያየ መረጃ በሠነዱ ውስጥ ለምን አሰፈረ? ምናልባት በሐረሪ ቋንቋ የሰፈረው ፈፅሞ ስህተት ቢሆንም እንኳ የእንግሊዘኛውን ያክል አስደንጋጭ ግዙፍ የታሪክ ብረዛ ያላካተተ ለዘብተኛ ግድፈት እንዲኖረው የተፈለገው ሆን ተብሎ ይሆን የሚል ጥርጣሬ አጫረብኝ ፡፡

ይልቁንም ቢሮው የአሹራ በዓል አከባበር ሥነ ሥርዓት በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብ ጥያቄውን ያቀረበው የብሔረሰቡን አዛውንት አነጋግሮና የኅብረተሰቡን አባላት አሳትፎ ባገኘው ይሁንታ መሆኑን ለመጠራጠር እንገደዳለን፡፡ ቢሮው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የቀረበውንና የራሱን ብሔረሰብ ታሪክ አዛብቶ የሚያቀርበውን የፈጠራ ትረካ ከመጠቀም ይልቅ በሐረሪ ቋንቋ የተጻፈውን በማቅረብ በሂደቱ አሳትፌአለሁ ላላቸው የብሔረሰቡ ተወላጆች ፊርማ ለማሰባሰብ ጥረት መደረጉን ያሳያል፡፡ እርስ በርሱ የሚቃረን ቅጂ ለምን ቀረበ የሐረሪውን ለአዛውንቱ ረዳት ፕሮፌሰሩ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ያዘጋጁትን ትረካ ደግሞ የውጭ ቋንቋ ለመረዳት ለሚችሉ የብሔረሰቡ አባላትና ሐረሪኛ ለማያውቁ ሌሎች ለሦስተኛ ወገኖች እንዳዘጋጀው ለመገመት አዳጋች አይሆንም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ሆን ተብሎ ታስቦበት የብሔረሰቡን ታሪክ ለማጠልሸትና ለመበረዝ የተከናወነ ተግባር ነው ወደሚል ድምዳሜ መምጣቱ አይቀርም፡፡ ለመሆኑ አያት ቅድመአያቶቹን የሚያዋርድ ተረት ባህሌ ነውና በዓለም ቅርስነት ይመዝገብልኝ ብሎ ማመልከቻ ያቀረበ ብሔረሰብ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ይኖር ይሆን?

በጽሑፌ መግቢያ ላይ እንደገለጽኩት በድርጅቴ በሐረሪ ብሔራዊ ሊግና የተለያዩ ቢሮዎችን እንዲመሩ በሹመት በሰየማቸውም ኃላፊዎች ላይ ጽኑ እምነት ያለኝ በመሆኑ ከዚህ ድምዳሜ ለመድረስ ያዳግተኛል፡፡ ሆኖም የብሔረሰቡን ባህልና የታሪክ ቅርሶች የመንከባከብ ኃላፊነት የተጣለበት ቢሮ ኃላፊነቱን የመወጣት አቅሙ ያሳስበኛል፡፡ የአቶ አዩብን ስህተት ያረመ መስሎት የዓሊ ናጂ ነው ቢልም ለረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ ታሪክን የማጠልሸትና የመበረዝ ድርጊት ሰለባ ሆኖ መገኘቱና በእንግሊዝኛና በሐረሪ ቋንቋዎች በቅፁ ውስጥ የሰፈረው ቅጂ ፍሬ ሃሳብ የተለያየ ሆኖ መገኘቱ፣ለረዳት ፕሮፌሰሩ የተቀነባበረ የሐረሪ ብሔረሰብ ታሪክ ብረዛና የማጠልሸት ሤራ ሰለባ መሆኑ ኃላፊነቱን የመወጣት አቅም በማጣቱ አሊያም ከዚህ በስተጀርባ አንድ የተለየ ተልዕኮ ያለው ቡድን ወይም ግለሰብ በውስጡ መኖሩን እንድንጠራጠር ያደርጋል፡፡ ከሁሉ በላይ

የተለየ ተልዕኮ ያለው ቡድን ወይም ግለሰብ ከዚህ የታሪክ ብረዛ ተግባር በስተጀርባ ካለና ያም የዋሃቢያ ዓላማ አስፈጻሚ ከሆነ ጉዳዩ አሳሳቢ ነው፡፡ በመሆኑም ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ቢሮው የፈጸመው ስህተት ሠፋ ተደርጎ ሲታይ በአሁኑ ጊዜ ዋሃቢያ በመላው ዓለም በሚገኙ አህሉ ሱና ወል-ጀማዓ ሱፊያ ሙስሊሞች ላይ የሚያካሄደውን የተቀነባበረ ዘመቻ በሐረሪ ሙስሊሞች ላይ በተለይም በሐረሪ ብሔረሰብ ላይ ለመከፈት እንዲችል ጠንካራ መደላድል ይፈጥርለታል፡፡ ማንም ሰው እንደሚረዳው አክራሪው የወሃቢያ / ሰለፊ ነኝ ባይ እምነት አራማጆች ከነቢያችን (ዓለይሂ ሷላቱ ወሰላም) በሳሃቦች ከዛም በየትውልዱ በታላላቅ የሃይማኖቱ መሻኢኾችና ዑለማዎች ቁርአንና ሀዲስን መሠረት ባደረገ ሰነዳዊ ማስረጃ ሳይቋረጥ እስከአሁን ያለውን እስላማዊ አካሄድና አሠራር ውድቅና ፍርስ በማድረግ የሚነሱ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ቀደምት ሃይማኖቱን ጠብቀው ያቆዩትን ሙስሊም ማህበረሰቦችን እንደ ኢጋሪና ከሃይማኖቱ እንደወጡ አሊያም እንደ መናፍቃን ስለሚቆጥሩ ጥንታዊ ሃይማኖታዊ ጽሑፎችን፤ መጻሕፍትን፤ሥነ-ሕንፃዎችና መካነ-መቃብሮችን በማውደምና በማጠፋት ተግባር ላይ ይሰማራሉ፡፡

የቢሮው ትረካ ወደድንም ጠላንም ላለፉት በርካታ ምዕተ ዓመታት ውስጥ የተጠናከረ የእስልምና መንፈሳዊ መዕከል ሆና የቆየችው ሀረር ውስጥ ከዝሙትም የከፋ ርካሽና ፀያፍ ሥነ-ምግባር የዳሸቀ፣ በመጠጥና በመጠጥ ሱስ ተገዢ የሆነ ብልሹ ባሕል ያለው ህብረተሰብ ነበር የሚል ድምዳሜ ማምራቱ ግልጽ ነው፡፡ መሠረተ ቢሱ የፈጠራ ታሪክም በተለይ ወጣቱ ትውልድ የቀድሞ አባቶቹና መንፈሳዊ መሪዎቹን ታሪክ እንዳይከተል ለማድረግ ለሚጥረው አክራሪ ኃይል ምቹ መደላደል በመፍጠር የእጅ አዙር እገዛ እንደሚሰጥ ደግሞ መገመት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡

በእስላማዊ እምነት መሠረታዊ ሕግጋትና መርሆዎች የዳበረ አንፀባራቂ ባህል ያለው ብሔረሰብ ያውም በእምነቱ በጣም ጠንካራ በነበረበት የቀድሞ ዘመን መጠጥ ይጠቅማል ወይስ አይጠቅምም በሚል አቋም የተከፋፈለና ልቅና ነውረኛ በሆነ የወሲብ ምግባር ውስጥ ተዘፍቆ እንደነበረ በሐሰት መዘገቡ ‘ቅድመ አያቶችህ ከእስልምና ሕግጋትና መርሆዎች ያፈነገጡ መናፍቃን ነበሩ’ ለሚለው የወሃቢ ስብከት የተረጋገጠ ‘ማስረጃ’ እያቀረበ አይደለም ለማለት እንዴት ይቻላል??

ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ ልዩ ትኩረት ሊሰጡት የሚገባው የሐረሪ ሕዝብ የአህሉ ሱና ወል-ጀማዓ ሡፊ መንገድ ተከታይ ፣የሐረር ከተማም በምሥራቅ አፍሪካ የእስላማዊ ትምህርት ማዕከል እንደነበረች በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመሰከረላት ፣ በተለይም የሐረር ከተማ ለእስልምና ሃይማኖት እውነተኛ አስተምሮት ተምሳሌት በመሆኗ የሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችና የተለያዩ እምነት ተከታዮች ተቻችለው የሚኖሩባት መሆኗ ታውቆ በዓለም ቅርስነት መመዝገቧ በመላው ዓለም ነውጥ በማካሄድ ላይ ለሚገኘው የዋሃቢያ ዘመቻ ዒላማ የሚያደርጋት መሆኑን ነው፡፡ ሐረር በወሊዮችና ተከታዮቻቸው ሱፊዎች ዘንድ ጃበሉል አውሊያእ (የወሊዮች ተራራ) ተብላ የምትታወቅ መሆኗ፣በውስጧና በዙሪያዋ ታላላቅ የወሊዮች መቃማት(አድባራት)የሚገኙ መሆናቸው የእስላማዊ ቅርሶች ፀር የሆኑትን ዋሃቢያዎች ያንገበግባቸዋል፡፡ በሌሎች ሀገሮች የወሊዮችን መቃብሮች እየቆፈሩ እንዳፈራረሱት በሐረርም የታላላቅ አውሊያዎችን መቃብሮችና አድባራት ማፈራረስ ዐቢይ ዓላማቸው ያደርጋሉ፡፡ ለዚህ ዓላማቸው ማሳኪያ አስቀድሞ የብሔረሰቡን ታሪክ ማጠልሸትና ለታሪካዊ ቅርሶቹ እንዳይቆረቆር ማድረግን አቅደው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ይህ ደግሞ በሌሎችም ሀገሮች ያከናወኑትና በማከናወን ላይ ያሉት ድርጊት ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላይ የተጠናከረ ዘመቻ የሚያካሄደውና በሀገሪቱ ውስጥ ሽብር ለመፍጠርና ሰላምን ለማናጋት በልዩ ልዩ ዘዴ የሚንቀሳቀሰው ዋሃቢያ ከላይ የተጠቀሰውን በብሔረስቡ ተወላጆች በሐረሪ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የባህል፣የቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም ቢሮና በረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ የተፈጠረውን የታሪክ ብረዛ አጉልቶ ከመጠቀም አይቦዝንም ፡፡

በበኩሌ የብሔረሰቡን ባህልና የታሪክ ቅርሶች የመንከባከብ ኃላፊነት የተጣለበት ቢሮ እርስ በርሱ የሚጋጭ ተረት እያቀረበ ታሪክን እየበረዘ በአንድ ራስ ሁለት ምላስ ሆኖ መገኘቱ ቢያሳስበኝም ከዚህ ጥፋቱ ታርሞ እውነተኛውን የብሔረሰቡን ታሪክ እንዲያስመዘግብ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡ አሁንም በድርጅቴ በሐረሪ ብሔራዊ ሊግና በመሪዎቼ ላይ ያለኝ እምነት ሙሉ በሙሉ ተሸርሽሮ ያላለቀ በመሆኑ በቢሮው የተፈጠረው ስህተት ታርሞ እውነተኛው የብሔረሰቡ ታሪክ እንዲመዘገብ ያደርጋል የሚል እምነቴን እየገለጽኩ የቢሮውንም ስህተት ገምግሞ በፍጥነት እንደሚያርም እተማመናለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚ «ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ አለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሀል» የሚለውን የአበው ብሂል ለድርጅቴ ለሐረሪ ብሔራዊ ሊግና ለመሪዎቼ ማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡

የተፈጠረው ታሪክን የማጠልሸትና የመበረዝ ድርጊት የሰው ልጆች ሁሉ ሰብዓዊ ሙብትና ብልጽግና ፀር ለሆነው ለሰለፊ ነኝ ባይ ለዋሃቢያ አክራሪ መጠቀሚያነት እንዳይውል ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ ግድፈቱ በወቅቱ ይታረም ዘንድ የሚመለከታቸው የተለያዩ የፌዴራል መንግሥቱ አካላትም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው የብሔረሰቡ ታሪክ ሳይበረዝ በትክክለኛ መልኩ እንዲመዘገብ ያደርጉ ዘንድ አሳስባለሁ፡፡

በመጨረሻም የብሔረሰቡ ተወላጆችም በፖለቲካ ድርጅት አባልነት ሳይከፋፈሉ ጉዳዩን በንቃት እንዲከታተሉትና ጨዋነት በተሞላበት ሁኔታ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ወገኖች ላይ ሕዝባዊ ጫና እንዲያደርጉ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ሁሉም በየሥራ ድርሻው ለሐረሪ ብሔረሰብ እውነተኛ ታሪክ ዘብ ይቁም እላለሁ፡፡